የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 31
ADDIS ABABA, 9th July, 2024

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፱/ ፪ሺ፲፮

በኢትዮጵያ እና በጆርዳን መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመ የመግባቢያ ሰነድ ማጽደቂያ አዋጅ
………………………………………......ገጽ ፲፭ሺ፮፻፲

## Content

Proclamation No. 1319/2024

Memorandum of Understanding between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Hashemite Kingdom of Jordan on the Employment of Ethiopian Workers Ratification Proclamation……
…………………………...……………Page 15610

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፱/ ፪ሺ፲፮

### በኢትዮጵያ እና በጆርዳን መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመ የመግባቢያ ሰነድ ማጽደቂያ አዋጅ

በኢትዮጵያ እና በጆርዳን መካከል የቆየውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር በማስፈለጉ፤

በጆርዳን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ሕጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው እና መብትና ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ በአገራቱ ፍላጎት ያለ በመሆኑ፤

ይህንን የመግባቢያ ሰነድ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እ.ኤ.አ. ጁላይ ፲፪ ቀን ፪ሺ፳፫ የፈረመው በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1319/2024

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE MEMORANDUM OF UNDERSTANDING BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE HASHEMITE KINGDOM OF JORDAN ON THE EMPLOYMENT OF ETHIOPIAN WORKERS

**WHEREAS**, to further strengthen existing bilateral relation between Ethiopia and Jordan;

**WHEREAS**, a desire exists for Ethiopian workers in Jordan to have a legal framework and to protect their rights;

**WHEREAS,** the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has signed the said Memorandum of Understanding on 12 July 2023;

ይህን ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፲፯ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ እና በጆርዳን መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመ የመግባቢያ ሰነድ ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፱/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>**

በኢትዮጵያ እና በጆርዳን መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

**፫. <u>አስፈጻሚ አካል</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ እና በጆርዳን መካከል በስራ ስምሪት ዘርፍ የተፈረመውን የመግባቢያ ሰነድ የማስፈጸም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**WHEREAS**, the House of peoples' Representa tives of the Federal Republic of Ethiopia has ratified said Memorandum of Understanding at its session held on the 14th day of March 2024;

**NOW, THERERORE**, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "Memorandum of Understanding between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Hashemite Kingdom of Jordan on the Employment of Ethiopian Workers Ratificatin Proclamation No 1319/2024".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

Memorandum of Understanding between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Hashemite Kingdom of Jordan on the Employment of Ethiopian Workers is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organ</u>**

The Ministry of Labor and Skills of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement the Memorandum of Understanding between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Hashmite Kingdom of Jordan on the Employment of Ethiopian Workers.

፬. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, On this 9th Day of July, 2024**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**